በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቀን ኅዳር 30 2012
Date
ቁጥር 6/0177/12
Ref.No.

**የጉምሩክ ስነስርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ**
**ባሉበት**

**ጉዳዩ:- የቀረጥ ነፃ መብትን ይመለከታል፡፡**

የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ለፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚያስመጣቸው የኢንቨስትመንት ዕቃዎችና መሣሪያዎች ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ፣ እንዲሁም ከኮርፖሬሽኑ ጋር የሥራ ውል የፈረሙ ሥራ ተቋራጮች የሚያስመጧቸው ዕቃዎች ለፕሮጀክቶቹ ማስፈፀሚያ የሚውሉ መሆናቸውን ኮርፖሬሽኑ ማረጋገጫ እየሰጠ ዕቃዎቹ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ በቁጥር ታ/ከ/ቀ/5/397 በቀን 16/9/2003 ዓ.ም. እና በቁጥር ቀ/ነ/ተ/14/619 በቀን 18/8/2005 ዓ.ም. በተፃፉ ደብዳቤዎች በተላለፈው መመሪያ መሠረት ተቋራጮች የሚያስመጧቸውን ዕቃዎች ለፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ የሚውሉ መሆናቸውን ኮርፖሬሽኑ ማረጋገጫ እየሰጠ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ጥያቄ ቢያቀርቡም በተሻሻለው የጉምሩክ አዋጅ መሠረት ኮርፖሬሽኑ ለሚያስገነባቸው ፕሮጀክቶች የቀረጥ ነፃ መብት እንዳለው በአዲስ መልክ ተጠቅሶ ካልተፃፈ በስተቀር ከዚህ ቀደም በነበረው አሰራር ሊስተናገዱ እንደማይችሉ የተገለፀላቸው በመሆኑ ለኮሚሽናችን ማብራሪያ እንዲሰጥላቸው በቁጥር 1.5/613/33/12 በቀን 9/3/2012 ዓ.ም. መጠየቃቸውን ገልፆ፣ ለኮርፖሬሽኑ የተሰጠው የቀረጥ ነፃ መብት ከላይ ቀንና ቁጥሩ በተገለጸው ደብዳቤዎች የተላለፉት መመሪያዎች በሌላ መመሪያ እስካልተሻሩ ድረስ አፈፃፀማቸው የሚቀጥል መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ታ/ክ/ቀ/5/121 በቀን 17/3/2012 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ አሳውቆናል፡፡

ስለሆነም ከኢ.ፌ.ደ.ሪ. ገንዘብ ሚኒስቴር በተገለፀው መሠረት በቁጥር ታ/ከ/ቀ/5/397 በቀን 16/9/2003 ዓ.ም. እና በቁጥር ቀ/ነ/ተ/14/619 በቀን 18/8/2005 ዓ.ም. የተላለፈው ውሳኔ በሌላ ያልተተካ ወይም ያልተሻረ በመሆኑ ተገቢው የጉምሩክ አገልግሎት እንዲሰጥ እያሳሰብኩ፣ ለአፈፃፀም ያመች ዘንድ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የተላከውን ደብዳቤ 1 ገጽ ኮፒ አባሪ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን ልከናል፡፡

ከሠላምታ ጋር

[illegible] ጫኔ አበበ
የጉምሩክ ኦፕሬሽን
ዘርፍ ም/ኮሚሽነር

አባሪ:- 1 ገጽ

ግልባጭ/

- ለጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጽ/ቤት /ከነ አባሪ/
- ለጉምሩክ ህግ ተገዥነት ዘርፍ ጽ/ቤት /ከነ አባሪ/
- ለዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት /ከነ አባሪ/
  ጉምሩክ ኮሚሽን



+251 116 62 98 00
+251 116 62 98 19
2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

ለፅ/ከመዝገብ ቤት 94

ጉ-ክፍ 721
24-3-2012

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር
Ref.No ዝ/ን/ቃ/ሰ/121
ቀን
Date 17/3/2012

ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን የባቡር መስመሮችን ለመገንባት ከተለያዩ የውጭ አገር የሥራ ተቋራጮች ጋር ውል ተፈራርሞ የግንባታ ሥራውን እያከናወነ እንደሚገኝ፣ ከዚህ ቀደም በመ/ቤታችን በተላለፈው መመሪያ መሠረት ኮርፖሬሽኑ ለፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የሚያስመጣቸው የኢንቨስትመንት ዕቃዎችና መሳሪያዎች ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ አገር እንዲገቡ እንዲሁም ከኮርፖሬሽኑ ጋር የሥራ ውል የፈረሙ የሥራ ተቋራጮች የሚያስመጧቸው ዕቃዎች ለፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ የሚውሉ መሆናቸውን ኮርፖሬሽኑ ማረጋገጫ እየሰጠ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ጥያቄውን ለመ/ቤታችሁ ቢያቀርብም በተሻሻለው የጉምሩክ አዋጅ መሠረት ኮርፖሬሽኑ ለሚያስገነባቸው ፕሮጀክቶች የቀረጥ ነፃ መብት እንዳለው በአዲስ መልክ ተጠቅሶ ካልተፃፈ በስተቀር ከዚህ ቀደም በነበረው አሰራር ሊስተናገድ እንደማይችል የተገለፀለት መሆኑን በመጥቀስ ስለመብቱ አፈፃፀም ለመ/ቤታችሁ ማብራሪያ እንዲሰጥለት በ09/-03/2012 ዓ.ም በቁጥር 1.5/613/33/12 በተፃፈ ደብዳቤ ጠይቋል፡፡

የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ለፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚያስመጣቸው የኢንቨስትመንት ዕቃዎችና መሣሪያዎች ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ አገር እንዲገቡ፣ እንዲሁም ከኮርፖሬሽኑ ጋር የሥራ ውል የፈረሙ ሥራ ተቋራጮች የሚያስመጧቸው ዕቃዎች ለፕሮጀክቶቹ ማስፈፀሚያ የሚውሉ መሆናቸውን ኮርፖሬሽኑ ማረጋገጫ እየሰጠ ዕቃዎቹ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ አገር እንዲገቡ መ/ቤታችን በ16/09/2003 በቁጥር ታ/ከ/ቀ/5/397 እና በ18/08/2005 በቁጥር ቀ/ነ/ተ/14/619 በተፃፉ ደብዳቤዎች መመሪያ ማስተላለፉ ይታወቃል፡፡ በእነዚህ መመሪያዎች መሠረት ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደውን የቀረጥ ነፃ መብት የሚያስቀር ተለዋጭ መመሪያ በመ/ቤታችን አልተላለፈም፡፡

ስለዚህ ለኮርፖሬሽኑ የተሰጠውን የቀረጥ ነፃ መብት አስመልክቶ ከላይ ቀንና ቁጥሩ በተገለጹት ደብዳቤዎች በመ/ቤታችን የተላለፉት መመሪያዎች በሌላ መመሪያ እስካልተሻሩ ድረስ አፈፃፀማቸው የሚቀጥል መሆኑን እየገለፅን ኮርፖሬሽኑ የሚያቀርበው ጥያቄ በዚሁ መሠረት እንዲስተናገድ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ፣
ለኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

Lerrer/Tw/

Tel 251-11-155 24 00,22 66 98 P.O.Box 1905,1037 Fax 251-11-156 01 24,55 14 96 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
251-11-155 00 81,83 86 89 251-11-155 11 38 Addis Ababa-Ethiopia